# በጉጂ ዞን ውስጥ በሚኖር የጌዴዖ ብሔረሰብ አናሣ ቡድን ላይ ተነጣጥሮ የተፈጸመ ጥቃትና የመብት ጥሰት

## የጌዴዖ ብሔረሰብ አናሣ ቡድን በጉጂ ዞን (የኋላ ታሪክ)

በአሁኑ ወቅት በኦሮሚያ ክልል የጉጂ ዞን የሚባለው ቀደም ሲል የጀምጀም አውራጃ በመባል ይታወቅ ነበር። የዞኑ ዋና ከተማ ክብረመንግሥት ነው። ክብረመንግሥት መዳረሻ ላይ አፈራራ የሚባል ዳገት አለ። በአፈራራ ዳገት ላይ (አዶላ ረዴ ወረዳ፣ አፈራራ ቀበሌ ገበሬ ማኅበር) እንዲሁም ቦሬና ሱኬ በሚባሉ አካባቢዎች መሀል፣ ወቲቆ ራሳና ወቲቆ ሹር ቀበሌ ገበሬ ማኅበራት ውስጥ የጌዴዖ ብሔረሰብ አባላት ሰፍረው ለረዥም ዘመኗየኖ ሩ ነው። ዛሬ የጉጂ ዞን በተባለው በዚህ ሥፍራ የጌዴዖ ብሔረሰብ ዓባላት ያላቸው ቆይታ በአሁኑ ወቅት እስከ አራት ትውልድ እንደደረሰ ይነገራል።

አካባቢው በአጠቃላይ በጣም ዳገታማና ወጣ ገባ የበዛበት እንዲሁም የተፈጥሮ ደን በስፋት የሚገኝበት ነው። ድሮ ቀለል ያሉ አማራጮች ለነበሯቸው የጉጂ ብሔረሰብ ዓባላት ለኑሮና ለሥራእምብዛም ተመራጭ አልነበረም። አነስተኛ ቁጥር ከነበራቸው የጉጂ አሮሞዎች በስተቀር ማንም ያልሠፈረበት ቦታ ነበር። ስለዚህ ጥቂት የጌዴዖ ብሔረሰብ ዓባላት ከዓፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ጀምሮ ወደአካባቢው በመሄድ ሊሰፍሩ ችለዋል። የማኅበረሰቡ ዓባላት ቁጥር በሂደት ጨምሮ በአሁኑ ጊዜ 767 አባወራዎች ደርሷል። የጌዴዖ ማኅበረሰብ አባላት በቦታው ከሠፈሩበት ወቅት አንስቶ የግብርና ሥራ በመጀመር ቡና፣ እንሠትና ጫት የመሣሰሉትን በማልማት ኑሮአቸውኗየመ ሩ ይገኛሉ። በወታደራዊው መንግሥት ዘመን፣ የማኅበረሰቡን መኖሪያና ንብረት ጨምሮ ሥፍራው በደን አካባቢነት እንዲከለል ተደርጓል። ይሁን እንጂ በወቅቱ ህዝቡ ባቀረበው ጥያቄ መሠረት ደኑን ሣይነካ ይዞታውን (መኖሪያውን፣ ማሣና ሌላም ንብረቱን) በነበረበት ሁኔታ እንዲጠቀምበት ተፈቅዶለታል። በዚህ መሠረት ህዝቡ ተገቢውን ግብር ለመንግሥት እስከአሁን ድረስ እየገበረ መቆየቱን የማኅበረሰቡ ተወካዮች ገልጸዋል። ይህ አጭር ዘገባ የተጠናቀረው ጉዳዩን በቀጥታና በቅርብ ከሚያውቁ የጥቃቱ ሠለባዎችና ሌሎችም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በተደረገ ረዥምና ተደጋጋሚ ውይይት ላይ ተመሥርቶ ነው። 700 የሚደርሱ የቤተሰብ ኃላፊዎች ፊርማቸውን ያኖሩበትን አቤቱታም ለማየት ይቻላል።

## በማህበረሰቡ ዓባላት ላይ የተፈጸመ የመብት ጥሰት

በጉጂ ዞን በአዶላ ረዴ ወረዳ የሚኖሩ የጌዴዖ ማኅበረሰብ አባላት፣ ከጥቅምት 1 እስከ 6 /2003 ዓ.ም. ባሉት ቀናት ውስጥ፣ ብዛትና ግምቱን በትክክል ሊገልጹ የማይችሉት፣ ለምግብነትና ለገቢ ማግኛ የሚጠቀሙበት የቡና ተክል (ፍሬውእንደያዘ)፣ እንሰት፣ ሙ ዝና ጫት ተጨፍጭፎባቸዋል። በተጨማሪም ለምግብነት በተዘጋጀ ቆጮ ላይ አፈር በመጨመር እንዳይጠቅም አድርገው እንዳበላሹባቸውና በዚህም ሣቢያ በርካታ የማኅበረሰቡ አባላት ለረሐብ እንደተዳረጉ ተጠቂዎቹ በምሬት ገልጸዋል። ተጎጂዎቹ ጥቃቱ እንደተፈጸመባቸው ወዲያውኑ የተጨፈጨፈባቸውን ሰብልና አትክልት ናሙናውን በመያዝ ለጉጂ ዞን አዶላ ረዴ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት አቤቱታለማቅረብ በብዛት ሆነው ጉዞ ለመጀመር ሞክረው ነበር። ነገር ግን ገና ሳይንቀሳቀሱ የፌዴራል ፖሊስ አድማ በታኝ ኃይል ከሥፍራቸው ደርሦ “የትም አትሄዱም” በሚል በሰላማዊ አቤቱታ አቅራቢው ህዝብ ላይ በአስለቃሽ ጭስና በጥይትም ቃጀበ ከፍተ ኛ ድብደባ ፈጽሞባቸዋል። በውጤቱም በርካታ ንጹኃን ዜጎች ቆስለዋል፣ ተጎድተዋል። አቤቱታ ማቅረብ እንደጥፋት ተቆጥሮ ዘጠኝ ሰዎች ታስረዋል። እንደሰለባዎቹ ገለጻ፣ ችግሩ በተከሰተበት ሥፍራ የማይኖሩና በወቅቱም በአካባቢው ያልነበሩ ሰዎች ሣይቀሩ፣ የጌዴዖ ብሔረሰብ ተወላጅ በመሆናቸው ብቻ ለእሥር ተዳርገዋል። በዚህ ዓይነት ከታሠሩት መካከል የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህር የሆኑት መምህር ብርሐኑ ገዴ ይገኙበታል።

በተመሣሣይ ሁኔታ አንዳንድ አነስተኛ ባለሐብቶች ከመኪናቸው ጭምር ታስረው የዚህ በጌዴዖ ማኅበረሰብ ላይ ያነጣጠረው ዘረኛ ጥቃት ሠለባ ሆነዋል፡፡

ከዚህ ሁሉ የከፋ ነው የተባለው ዘረኛ ጥቃት ደግሞ በአካባቢው የሚኖሩ የጌዴዖ ማኅበረሰብ አባላት መኖሪያቸውን ለቀው እንዲሄዱ እየተደረገባቸው ያለው የማስፈራራትና የማስገደድ ድርጊት ነው፡፡ ይህ ግፊት እስከአሁንም ድረስ እንደቀጠለ መሆኑ ም ታውቋል፡፡ ሕዝቡ ይህን ሁሉ ጥቃትና አፈና እንደምንም ተቋቁሞ፤ ጉጂ ዞን መስተዳድር ጽ/ቤት ድረስ በመሄድ አቤቱውን አቅር ቧል፡፡ ሆኖም የዞኑ አስተዳደርኃላፊዎች ለአቤቱታው ተገቢውን ትኩረት ባለመስጠታቸው እስ ካሁን ለችግሩ መፍትሔ አልተገኘም፡፡

ከተለያዩ ምንጮች ለማጣራት እንደተሞከረው፤ ይህ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰትና ጥቃት ከአስከፊነቱም ባሻገር በጣም ግራ የሚያጋባ ሌላም ባሕርይ አለው፡፡ ይኸውም ጥቃቱ መንግሥታዊ ጥቃት መሆኑ ነው፡፡ በነዚህ የጌዴዖ አናሳ የማኅበረሰብ ቡድን አባላት ላይ ጥቃቱን እያደረሱባቸው ያሉት በአካባቢው የሚኖሩት የጉጂ ኦሮሞ ማበረሰብ አባላት አይደሉም፡፡ ይልቁንም የመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች ማለትም የአካባቢው ታጣቂዎችና የፌዴራል ፖሊስ አባላት ናቸው፡፡

## ማጠቃለያ

የጥቃቱ ሰለባዎች ችግራቸውን ከዞኑ መስተዳድርም አልፈው ለልዩ ልዩ የደቡብ ክልል መስተዳድር አካላት አመልክተዋል፡፡ ነገር ግን መፍትሔ ለማግኘት አልቻሉም፡፡ በመጨረሻም ተጎጂዎቹ፤

> "አምርተን/ሠርተን መብላትእንዳንችል፤ ል ጆቻችን እንዳይማ ሩና በመንደራቸው እንዳይጫወቱ፤ ሴቶቻችን እንዳይገበያዩና ወደሥራ እንዳይወጡ፤ በአጠቃላይ ተወልደን ባደግንበት፤ የልጅ ልጅ ባየንበትና እንደየአቅማችን ንብረት ባፈራንበት አካባቢያችን በሠላም ወጥተን እንዳንገባና በሠላም ሠርተን መኖር እንዳንችል ከአቅማችን በላይ የሆነ ተጽዕኖ እየተፈጸመብን ነው፡፡ በመሆኑም የሚመለከታችሁ ሠላም፤ ፍትሕና እኩልነት ወዳድ የሆናችሁ ወገኖች ሁሉ ለጉዳያችን ትኩረት ሰጥታችሁ ችግራችንን በማጣራት፤ ችግ ሩ ከዚህም በላይ የከፋ ደረጃ ላይ ከመድረሱ በፊት፤ ፈጣን ምላሽ እንድናገኝ እንድትረዱን አቤታችንን እናቀርባለን" በማለት አቤቱታቸውን አሰምተዋል፡፡

## _ማስታወሻ_

*ስለችግሩ ተጨማሪ ማብራሪያ የሚፈልጉ ወገኖች፤ ጉዳዩ ታብቀጥሚመለከታቸውን የማህበረሰቡን ተወካዮችና በየደረጃው የሚገኙትን የአካባቢ መስተዳድር ኃላፊዎችን በሚከተሉት የስልክ አድራሻዎቻቸው ማግኘት ይችላሉ፡፡*

1ኛ) _የጥቃቱ ሰለባ የሆነው የጌዴዖ ማኅበረሰብ ተወካዮች:_

- *1.1 አቶ ኢያሱ ሮቤ* — *ስልክ - +251-0910707197*
- *1.2 አቶ ተፈራ አዱኅ* — *ስልክ - +251-0911965197 ወይም +251-046335035*

2ኛ) _የአካባቢው የመንግሥት ኃላፊዎች:_

- *2.1 አቶ ገናሌ (የአዶላ ረዴ ወረዳ አስተዳዳሪ):* — *ስልክ - +251-0463350002*
- *2.2 አቶ ሐረዴ ገመዳ (የጉጂ ዞን የግጭት መከላከልና መፍታት ዋና የሥራ ሒደት ኃላፊ)* — *ስልክ - +251-0916850490*
- *2.3 አቶ ሑሴን ዱቤ (የጉጂ ዞን የግጭት መከላከልና መፍታት የሥራ ሒደት ባለሙያ)* — *ስልክ - +251-0464452014*